ከይኩኖ መሰፍን sgbtsait@gmail.com

# ተቃዋሚ ሐይሎችና የዜሮ ድምር የፓለቲካ ጨዋታ

ከሁሉም በፊት የተቃውሞ ጎራውን በተነሳ ቁጥር ሁሉ ጊዜ በአእምሯችን ድቅን የሚሉት ለህዝባችው የተሻለ ለውጥ ለማምጣት ሲሉ ራሳቸውን እንደሻማ እየቀለጡ ሲታገሉ በክብር ስላለፉ ሰማእታትን ነው። የተቃውሞ ትግሉ ላለፉት በርካታ ዓመታት እየወደቀም እየተነሳም ቢሆን ለነፃነት፣ ለፍትሕ፣ ለዴሞክራሲና ለሕግ ልዕልና ሲባል በገንዘብ የማይተመን ክቡር የህይወት ዋጋ የተከፈለበት ስለሆነ ምንም ጊዜም የማይረሳ ወርቃማ የታሪክ አሻራ ጥሎ አልፏል። ስለሆነም በትግሉ ሂደት የወደቁትን ጀግኖች ሰማእታት ወገኖቻችንን ሁሉ ክብርና ምስጋና ይድረሳቸው እላለሁ። ዛሬም እንደትላንቱ መብታችንን ይከበር ስላሉ ብቻ በሽዎች የሚቆጠሩ በየእስር ቤቱ ታጉረው የሚገኙት ታጋይ ወጣቶች፣ ጋዜጠኞች፣ የፓለቲካ ድርጅቶች አባላትና መሪዎች፣ ከቤት ንብረታቸው እየተፈናቀሉ ለስደትና ለእንግልት የተዳረጉ ወገኖቻችንና እንዲሁም በህዝቡ ጉያ ሆነው በፅናት በመታገል ላይ የሚገኙትን ታጋይ ወንድሞቼና እህቶቼ ሁሉ በዚሁ አጋጣሚ ያለኝን ክብርና አድናቆት ልገልፅ እወዳለሁ።

የዛሬውን ክፍል ሁለት ፅሑፌ አላማም በየጊዜው የሚከፈለውን ክቡር መስዋእትነት ውጤታማ እንዳያወጣ እንቅፋት በመሆን በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ደጋግመን እንደምንወቅሰው ሁሉ በተቃዋሚ የትግል ጎራው አካባቢ ያለው የተመሰቃቀለና የተጠላለፈ አካሄድም ለሀገርና ለህዝብ ጥቅም የማይበጅ ስለሆነ ተስተካከሉ ብሎ ገንቢ የሆነ የእርምት ሐሳብ መስጠት፣ ጥሩ የሰራው ደግሞ ጥሩ ሰርተሃል ብለን መደገፍና ማበረታት የሰለጠነ የዴሞክራሲ ባህል ብቻ ሳይሆን ትግሉን ተጠናክሮ ወደፊት ለመግፋት እንዲችል ትልቅ አስተዋፆ ያለው ስለሆነ መለመድ አለበት ከሚል በጎ መንፈስና አመለካከት በመነሳት የተሰማኝንና የታዘብኩትን ነፃ ሃሳብ አጠር ባለመልኩ እንደሚከተለው ለማቅረብ ነው።

ወደ ዋናው ዝርዝር ሐተታ ከመግባቴ በፊት ለመነሻነት እንዲመቸኝ አንዳንድ ጥያቄዎችን ላንሳና ወደ ቀጣዩ ነጥብ ልለፍ። ተደጋግሞ እንደሚሰማው "በግልም ሆነ በቡድን በተቃዋሚነት ከተሰለፍነው ሐይሎች ውስጥ አብዛኞቻችን በስልጣን ላይ ያለውን ስርዓት በአምባ ገነንነት: በፀረ አንድነት: በሀገር ክሕደት፣ በከፋፋይነት: በዘረኝነት፣ በጠባብ ቡድናዊነት፣ በምሕዳረ ብልሹነት፣ በአፋኝነትና በሙሱና የምንፈርጀው ጥቂቶች አይደለንም። መቃወማችን በራሱ ስህተት አይደለም። ሀገርንና ህዝብን ማእከል አድርጎ የሚቀርብ ተቃውሞ ከሆነ ተገቢ ነው ብዬ አምናለሁ። ነገር ግን ለህዝቡ የተሻለ አማራጭ የፓለቲካ ሐይሎች ነን የምንል ከሆነ ደግሞ ከህወሓት/ኢሕአዴግ የምንለይበት መሰረታዊ ባህሪያትና ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ምንድን ናቸው።? ለመሆኑ ለ90 ሚሊዮን ህዝብ የሚሆን የአላማ ጥራት; የአላማ ፅናት; የአላማ አንድነት; የውስጠ ፓርቲ የመሪነት ሚናና ዲሲፒሊን (coherence and leadership Integrity)፣ እንዲሁም ህዝቡን አስተባብሮ ለድል ሊያበቃ የሚያስችል ህያው የሆነ ስትራተጂ ያለን ተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶችስ ስንቶቻችን ነን።? በስልጣን ካሉት መሪዎች በተሻለ መንገድ ከግል ጥቅም : ከስልጣን ጥመኝነት: ከጠባብ ቡድናዊ አመለካከት፣ ከኋላቀር የፓለቲካ ባህልና መጠላለፍን ሰብረን በመውጣት የጋራ ሀገራዊ ጉዳይን በማስቀደም በፅናት የቆምነው የፓለቲካ መሪዎች ስንቶቻችን ነን።? ለምሳሌ እንበል በስልጣን ላይ ያለው መንግስት በራሱ ውስጠ ቅራኔ ድንገት ነገ ቢፈረካከስ የሀገራችን ዕጣ ፋንታስ ምንድን ነው የሚሆነው? ህዝባችንስ በማን እጅ ላይ ነው የሚወድቀው? ተቃዋሚ ድርጅቶችስ የህወሓት/ኢሕአዴግ መንግስትን ተክተን ሀገሪቱን በብቃት ለመምራትና የዴሞክራሲ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል የሞራል መሰረቱን፣ ዓቅሙን፣ ዝግጅነቱንና ንቃተ ህሊናውን አለን ወይ? በስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ከተቃዋሚዎች ስህተት ብዙ ይማራል። ተቃዋሚ ሐይሎችስ ከታሪክ፣ ከራሳችን ስህተትና ውድቀት የምንማረው መቼ ነው?" የሚሉትን ጥያቄዎች በብቃት መመለስና አለመመለስ የአንድ ተቃዋሚ ፓለቲካዊ ድርጅት ህላዌ የሚወስኑ ናቸው ብዬ አምናለሁ።

ጭቆናና አድልዎ እስካለ ድረስ ትግል የማያቋርጥ ሂደት መሆኑን ከታሪክ እንማራለን። ባሳለፍናቸው ዘመናት በየትግል ምዕራፉ በርካታ ድሎች እየተመዘገቡ መምጣታቸው ይታወሳል። ነገር ግን ዘላቂነትና አስተማማኝነት እንዳይኖራቸው ገና ለፍሬ ሳይበቁ በአቋራጭ በአፈ ሙዝ እየተነጠቁ ይኸውና ችግራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መጥቶ ዛሬም በመስቀለኛ መንገድ ላይ ቆመን እንገኛለን። ዛሬም ትግሉ እየወደቀ እየተነሳም ቢሆን ቢቀጥልም ውጤቱ እንደተለመደው የዜሮ ድምር የፓለቲካ ጨዋታ እየሆነ መምጣቱ አልቀረም። ለትግሉ መዳከም ትልቅ አስተዋፅዖ ካደረጉት መሰረታዊ ችግሮች ውስጥ ግዳማዊና ውስጣዊ ችግሮች ናቸው። ለምሳሌ ወደ ሩቅ ሳንሄድ ሻዕቢያ ራሱ በቁጥጥሩ ስር አድርጎ የሚያደራጃቸውን ቡድኖች እንኳን በአንክሮ ስንመለከት ዛሬም የትግል ኳሱ ዞሮ ዞሮ በነማን እጅ እንዳለ በግልፅ ያሳየናል።

## የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው (የነ ግንቦት 7 እና የሻዕቢያ መርህ አልባ ግንኙነት)

ሻዕቢያ ላለፉት አርባና ሐምሳ ዓመታ ሀገር በቀል ተቃዋሚ ሐይሎችን ለማዳከምና ሀገርን ለመበታተን ሲባል በኢትዮጵያውያን ትግል ላይ ሲጫወት የቆየውን አፍራሽ ሚና ስፍር ቁጥር የለውም። ዛሬም ከራሳችን ሳይወርድ ከአጋም እንደተጠጋ ቁልቋል ሀገራችን እየደማች እንድትኖር ተፈርዶባታል። በአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ የሚመራው ሻዕቢያ "ለኢትዮያውያን የመቶ ዓመት የቤት ስራ ሰጥተናቿል" ብሎ በአደባባይ እንደተናገረው ሁሉ ከተፈጠረባት ቀን አንስቶ እስከአሁንዋ ደቂቃ ድረስ ለግማሽ ክፍለ ዘመን ያህል ያለ መሰልቸት እንቅልፍ አጥቶ ሲያሰላስልና ሲያፈርስ የኖረው ኤርትራን ገንጥሎ የኢትዮጵያውያንን ጎሮሮ አንቆ ለመያዝ ብቻ ያለመ አልነበረም። ከኤርትራ መገንጠል በኋላም በአፍሪቃ ቀንድ ምን ዓይነት ኢትዮጵያ መሆን እንዳለባት ራሱ ወሳኝ አድርጎ በማሰብና

የጎበዝ አለቃ በመሆን ትልቅ አጀንዳ ቀርፆ ሲተገብረው ቆይቷል። ዋናው አላማው ኢትዮጵያ የምትባል ምድር ዳግም በኤርትራ ላይ ጥያቄ የማታነሳ፣ የተበታተነች፣ የተዳከመችና የተዋረደች ሀገር ሆና እንድትኖር ስለሆነ አሁንም በግልፅ እየተገበረው ይገኛል። በሌላ አነጋገር የነኢሳያስ ትልቁ ስጋት "በአፍሪቃ ቀንድ በኢኮኖሚም ሆነ በፓለቲካ የጠነከረች አንዲት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ከተረጋገጠች እንደፈለግን የምንበረቡራት አትሆንም። የኤርትራ ነፃነትንም ዋስትና አይነረውም" ከሚል የተዛባ ስሌት በመነሳት ሁሉ ጊዜ ሀገራችንን በስጋትና በጠላትነት ዓይን ይመለከቷታል። ይህንን ሰይጠናዊ አመለካከታቸውንና አፍራሽ አላማቸውን እውን ለማድረግ ደግሞ ካለፉት አርባና ሐምሳ ዓመታት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ኢትጵዮያን ለማዳከም ሲባል ሲተገብሩት የቆዩትን ስትራተጂ ከብዙ በጥቂት እንደሚከተለው ነው።

- ኢትዮጵያውያንን በኢትዮጵያውን እርስ በርስ በማጨፋጨፍና በማናቆር ሐይላቸውን እንዲዳከም ማድረግ ትልቁ አጀንዳቸው ነው
- ኢትዮያውያንን በተለያየ ስልት በማሰባሰብና በማደራጀት የኤርትራን ነፃነት ማጠናከሪያና መሳሪያ ሆነው እንዲያገለግሉ ማድረግ
- በኢትዮጵያ ምድር ሀገር በቀል የሆኑትን ተቃዋሚ የፓለቲካ ሐይሎች ትግል እንዳይጠናከር እርስ በርስ በማባላት ማዳከምና መበተን
- በሀገራችን ኢትዮጵያዊነት ብሄረተኝነት ስሜት ያላቸውን ዜጎች እንዳይጠነክሩ በረቀቀ መንገድ ማዳከምና ወኔያቸውን መስለብ
- የኢትዮጵያ አንድነት ለማፈራረስ ሲባል የግንጠላ ርእዮት ያላቸውን ቡድኖች እየመረጡ ማሰልጠን፣ ማስታጠቅና በኛ ላይ ማዝመት
- በኢትዮጵያውያን ላይ የብቀላ ጦርነት በመለኰስ ሀገራችን የህውከትና የግርግር አውድማ ሆና እንድትኖር ማድረግ
- ሌላ ቀርቶ ለነፃነታቸው ሲዋጉ የተማረኩትን ዜጎቻችን እንደ ባዕድ ወራሪ ወታደር በመቁጠር የቂም በቀል ባርነታዊ ስራ መፈፀም
- የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች የሆኑትን የነ ሊቢያ፣ ግብፅ፣ ሳውዲ ዓረቢና ሌሎች አክራሪ ሀገሮችን ወኪልና ደላላ በመሆን የሀገራችንን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ ሳይታክቱ ማመቻቸትና መዶለት
- ንፁሃን ዜጎቻችንን ከያሉበት እያፈኑ በመውሰድ ለኩላሊት ንግድ ፣ ለባርነታዊ ስራና ለሞት እንዲዳረጉ ሌት ተቀን መስራት
- በሀገራችን ጉዳይ ላይ በቀጥታ እጃቸውን በማስገባትና የራሳቸውን ሰዎች ሰርገው እንዲገቡ በማድረግ እንዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩትን አንዳንድ ኤርትራውያንና ከሻዕቢያ ጋር የትውልድ ሐረግ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ነን የሚሉ ሰዎች በጋሃድም ሆነ በስውር የእነሱ ፓሊሲና ስትራተጂ መሳሪያ ሆነው እንዲያገለግሉ ማድረግ፣ ወዘተ ወዘተ ናቸው።

የሻዕቢያ ባህሪይና ተግባር ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ ነገር ግን <u>የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው</u> ከሚል ቂም በቀል የወለደው ጭፍን ስሌት በመነሳት በነ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ የሚመራው ግንቦት 7 የህዝባችን ደመኛ ጠላት ከሆነው መንግስት ነኝ ባይ አምባገነን ጋር በመተባበር ኢትዮጵያን በትጥቅ ትግል ነፃ እናወጣለን በማለት አስመራ ውስጥ ቁጭ ብለው ጦርነት አውጇል። ይህ ዓይነቱ ውሳኔና የትግል መንገድ መምረጣቸው በደፈናው መብታቸው ነው ተብሎ የሚታለፍ ቢሆንም የተከተሉትን የትግል መስመርና እያደረጉ ያሉትን እንቅስቃሴ መዘዙ ሰላማዊ ትግላችንን የሚያዳክም ብቻ ሳይሆን የሀገራችን የወደፊት ዕጣ ፋንታም አደጋ ላይ የሚጥል ስለሆነ " ቤቱን ሳይቀጠል በቅጠል" ነውና ገና ስር ሳይሰድ መታረም አለበት ብዬ በማመን የበኩሌን ሃሳብ ለመስጠት ነው። " የሰጠኸው ሃሳብ ትክክል አይደለም " ብለው ትችት የሚያቀርቡልኝ ወገኖች ካሉ ደግሞ እኔም ሃሳባቸውን አከብራለሁ። ዋና ዋና የመቃወሚያ ነጥቦቼም የሚከተሉት ናቸው።

አንደኛ) እነ ግንቦት 7 የመረጡትን የትግል መንገድ የሀገራችን ነባራዊ ሁኔታና የህዝባችንን ክብር ፣ ቁስል፣ ስሜትና ፍላጎት ያላገናዘበ የቂም በቀልና የጭንቀት ውሳኔ እንጂ በጥልቅ ጥናት ላይ ተደግፎ ታስቦበት የመረጡት የትግል መንገድ አይመስለኝም። ለበርካታ ዓመታት ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር እየተባለ የጥይት ጭኾት የሰለቸውን ህዝብ ገና የቆሰለውን ልቡ ሳይሽር እንደገና ዛሬ ስለጦርነትና ስለትጥቅ ትግል ቢወራ ለሀገራችን ፋይዳ ይኖሯል የሚል እምነት የለኝም። ከደርግ ዘመን ጀምሮ እስካሁን ድረስ በተግባር ያየነው ተሞኩሮም <u>በጠመንጃ የመጣ ስልጣን መልሶ በጠመንጃ ሲጠበቅ</u> እንጂ ለህዝቡ ሰላምና ዴሞክራሲ ሲያጎናፅፍ አላየንም።

ሁለተኛ) እነ ግንቦት 7 ወደ ኤርትራ መጠጋታቸው በበለጠ ተጠቃሚ የሚሆነው ሻዕቢያ እንጂ ኢትዮጵያውያን አይደሉም። ሻዕቢያ እንደነ ግንቦት 7 እና ሌሎች የግንጠላ ሐይሎችን ሲያስጠጋ ለህዝባችን የዴሞክራሲ ለውጥ ለማምጣት አስቦ ሳይሆን ለሁለት ነገሮችን እንዲጠቀምባቸው ፈልጎ ነው። በአንድ በኩል ከቀናውና ከፍተት ካገኘ እነ አነግን በአቋራጭ ስልጣን ላይ ጎልቶ የረጅም ጊዜ ሕልሙን በሀገራችን ላይ ለመጫን ነው። ካልቀናው ደግሞ <u>በስልጣን ላይ ካለው ከህወሓት/ኢሕአደግ መንግስት ጋር እንደ መደራደሪያ መሳሪያ አድርጎ እንዲጠቀምባቸው</u> ነው። ይህ ዓይነቱ ስሌት ደግሞ ከአሁን በፊትም በተግባር የታየ ስለሆነ አዲስ ነገር አይሆንብንም።

ሶስተኛ) እነ ግንቦት 7 ሰላማዊና ሕጋዊ የትግል መንገዱን ትተው የትጥቅ ትግልን ለማካሄድ ወደ ሻዕቢያ የተጠጉበትን ሌላው ምክንያት <u>ምናልባት ህወሓት የመጣበትን የትግል መንገድ ተከትለን በመሄድ ስልጣን ላይ እንወጣለን</u> የሚል ስሌት ተነሳስተው ከሆነ ደግሞ በ21ኛ ክፍለ ዘመን ላይ ከሚኖሩት ፓለቲከኞች ፍፁም የማይጠበቅ ትልቅ የስትራተጂ ስህተት ይመስለኛል። ምክንያቱም ከሰላሳ ዓመት በፊት የነበረው ሁኔታና አሁን ያለው ነባራዊ ሁኔታ የሰማይና ምድር ልዩነት እንዳለው ለማወቅ የግድ ፊደል መቁጠርም አያስፈልግም። ዛሬ በትጥቅም ሆነ በስንቅ የሚረዳህ ህዝብና መንግስት ቀርቶ የምትደበቅበትን ጫካ እንኳን እየጠበበ መጥቷል።

ህዝባችንም እንደ ድሮ ምታ ነጋሪት ክተት ሰራዊት ብለህ በስሜት የሚነዳ አይሆንም። ህዝቡ ላለፉት አርባ ዓመታት ካሳለፋቸው ውጣ ውረድ ችግሮች ብዙ ተምሯል። ብዙ ቤት ፈርሷል። በአካባቢያችንና በዓለም ዙሪያ እየተካሄዱ ያሉት አውዳሚ ጦርነቶችንም ውጤታቸው ምን እንደሆነ በየቀኑ ያያል ይገነዘባል። ስለዚህ ዛሬ ህዝቡ ሲደግፍም በምክንያት ነው ሲቃወምም በምክንያት ነው። "የጨነቀው እርጉዝ ያገባል" ካልሆነ በስተቀር በአሁኑ ጊዜ ሻዕቢያን ነፃ ያወጣኛል ብሎ በማመን ጫካ የሚገባ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ይገኛል ብዬ ፍፁም አላምንም።

አራተኛ) ግንቦት 7 የራሱን ወገን ከሆኑት ከሰላማዊ ታጋይ ሐይሎች ጋር አብሮ ከመስራት ይልቅ በሰብአዊ ፈጡር ላይ በወንጀለኝነት (crime against humanity) ከተፈረጀው መንግስት ጋር መጎዳኘቱ በዓለም አቀፍ መድረኮችም ቢሆን ሕጋዊ ያልሆነ የትጥቅ ትግል የሚደገፍ አይደለም። የሽብርተኝነትን አደጋ በዓለም ህዝብ ዘንድ በተጠላበት ዘመን የትጥቅ ትግል መርጦ ጫካ መግባት ተቀባይነት እያጣና ጊዜው ያለፈበት ፋሽን እየሆነ የመጣበት ሁኔታ ነው የምናየው። ሻዕቢያም ይቅርና የሌላ ሀገር ህዝብ ነፃ ሊያወጣ ቀርቶ የራሱን ህዝብ እንኳን ወደ ባርነት የቀየረ መንግስት ነው። ለራሱ ህዝብ እንኳን ያልራራ ጨቋኝ መንግስት ነጋ ጠባ በጠላትነት ለሚመለከተው የኢትዮጵያ ህዝብ በጎ ነገር ያስባል ማለት ከእባብ እንቁላል እርግብ ይወለዳል ብሎ እንደመጠበቅ ያህል ነው የሚሆነው። ባህሪውንም አይፈቅድለትም። ስለዚህ በዓለም ማሕበረሰብ የተገለለና ከራሱን ህዝብ ጋርም የማይታረቅ ቅራኔ ውስጥ ገብቶ በጭንቀት ላይ ከሚገኘው አፋኝ መንግስት ጋር ሽሪክ ሆኖ መንቀሳቀስ ማለት የኢትዮጵያ ህዝብን ትግል መግደል ብቻ ሳይሆን ፍትሕና ነፃነት የጠማውን የኤርትራ ህዝብ ትግልም መፃረር ይሆላል።

አምስተኛ) አብዛኞቹ የነ ግንቦት 7 አመራርና አባላት ትላንት ህወሓት/ኢሕአዴግን በሀገር ክሕደት ሲኮኑኑት የነበሩት መሆናቸው የሚታወቅ ነው። ነገር ግን ዛሬ ከሀገራቸው ሉዓላዊነት፣ ብሄራዊ ጥቅምና ክብር በላይ ለሻዕቢያውያን ጥቅምና ድህንነት ጥብቅና በመቆም በተለይም ዘርና ቋንቋ እየለዩ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳቸውን ሲያራምዱ ማየቴ ይገርመኛል። ለምሳሌ በሻዕቢያ የሚደጎመው በአሜሪካ የሚገኘውና የግንቦት ሰባት ልሳን የሆነውን እሳት ራዲዮ ስንመለከት በአንድ በኩል በኢትዮጵያ ነፃ ሚዲያ የለም ታፍነናል እያሉ ሲናገሩ  ይሰማሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ለራሳቸው ሻዕቢያን የሚወቅስ ዜና ወይም ፅሑፍ ለመቀበል ቀርቶ ይባስ ብለው በየስብሰባው የኢሳያስን ስርዓት ሲያወዱሱና ሲያሞጉሱ ይሰማሉ። እነ ግንቦት 7 እና እሳት ራዲዮ በአንድ በኩል የህወሓት/ኢሕአዴግ መንግስትን እንቃወማለን እያሉ በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ የኤርትራ ህዝብ ደመኛ ጠላት የሆነውን አምባ ገነን የሻዕቢያ መንግንስት የሚያወድሱና ጥብቅና የሚቆሙ ከሆነ ታዲያ ማንን ነፃ ለማውጣት ነው ጫካ ገብተናል የሚሉን።? ስለዚህ እነዚህ ሐይሎች ህዝብን ነፃ የሚያወጡ ሳይሆን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እኛ ኢትዮጵያውያንን እርስ በራሳችን ለማባላት የተሰለፉ መሆናቸው ከተግባራቸው በላይ ሌላ ምስክር አይኖርም። በሰሜኑ ክፍለ ሀገራችን በየጊዜው ሻዕቢያ በሚያደራጃቸው ታጣቂ ስኳድ እየታፈኑ መረብ የሚሻገሩትን የንፁሃን ወገኖቻችን ደም የነማን እጅ እንዳለበትና ማን በተላላኪነት እያገለገለ እንዳለ እኮ ያዳባባይ ሚስጢር ከሆነ ቆይቷል።

ስድስተኛ)  እነ ግንቦት 7 "በኢትዮጵያ አፋኝ ስርዓት ስላለ ሰላማዊ ትግል አይቻልም" ብለው ደጋግመው ሲናገሩ እንሰማለን። በኢትዮጵያ ጨቋኝ ስርዓት መኖሩ ለኛ አዲስ ዜና አይደለም። ነገር ግን እነ ዶክተር ብርሃኑ መመለስ የሚገባቸው ጥያቄዎች ሰላማዊ ትግሉ ይስራ አይስራ መቼ ተሞኮረና።? የትግል ሜዳውን ጥሎ ወደ ስደት መሄዱንስ የሚጠቅመው ማን ነው? የትግሉን ባለቤትና የሰርዓቱን ግንባር ቀደም ገፈት ቀማሹ የሆነ ሰፊው ህዝብ ነው ብለን የምናምን ከሆነስ በቅርብ ሆኖ የሚያስተባብረው ማን ይሁን? የሚሉት ናቸው። አዎ!! ሰላማዊ ትግሉ ጥበብ፣ ሀቀኝነትና ቁርጠኝነት ያለው ሰው ነው ያጣው እንጂ ለለውጥና ለትግል ዝግጁ የሆነ ህዝብ እንዳለ እኮ በተግባር እየታየ ነው። ተባብረው በአንድነት ከሰሩና ሀገራዊ ጥቅምን በማስቀደም በቅንነት ከተንቀሳቀሱ ደግሞ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል እኮ በ97ቱ የቅንጅት ጊዜ በተግባር ታይቷል። በወሳኝ መልኩ ቅንጅትን ለውድቀት የተዳረገው እኮ መንግስት ከወሰዳቸው እርመጃዎች ባሻገር በራሱ በውስጡ በተፈጠረው የወንበር ጉተታ ምክንያት እንጂ በሀገራችን ሰላማዊ ትግል ስለማይቻል አይደለም። ታዲያ!! እነ ግንቦት 7 ሰፊ ሀገርንና ለለውጥ ዝግጁ የሆነ 90 ሚሊዮን ህዝብን በሰላማዊ መንገድ አስተባብረው በጋራ ለማታገል የሚያሰችል ሀቀኛ ራእይ፣ የሰለጠነ የአመራር ጥበብ፣ ድርጅታዊ ብቃትና የአላማ ፅናት ያላገኙ ነገር ግን ዛሬ የትጥቅ ትግልን በመምረጥ ጫካ ወርደው ውስብስብ መስዋእነትን አልፈው ስልጣን ላይ ለመውጣት የሚያስችላቸው ሞራሉም፣ ራእዩም፣ ብቃቱንና ፅናቱን ከየት አገኙት።? ስለዚህ እነ ግንቦት 7 ራሳቸውን ተቃዋሚ የፓለቲካ ሐይል ነን ይበሉ እንጂ በተግባር ሲታዩ ወደዱም ጠሉም በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የሻዕቢያን አላማ ከማራመድ አልፈው በብዙ መመዘኛዎች የለውጥ ሐይል መሆን አይችሉም። ጎበዝ!! የለውጥ ሐይል ለመሆን እኮ ቢያንስ የሀገሪቱን ነባራዊ እውነታ በጥልቀት መረዳትና የህዝቡን ልብ ትርታ ማግኘት የግድ ይላል።

## ተቃዋሚ የፓለቲካ ሐይሉን ያዳከሙት ውስጣዊ ችግሮች

የተቃውሞ ሐይሉን መዳከም ምክንያት ከሆኑት ሌሎች መሰረታዊና ዓበይት ችግሮች ውስጥ አንዱ በራሳቸው በተቃዋሚ የፓለቲካ ሐይሎች ያለው ውስጣዊ ችግር የወለደው አደጋ ነው። ይህ ስር የሰደደ ችግር በሚመለከት ህዝቡም ሆነ የተለያዩ ሀገር ወዳድ ወገኖች መፍትሄ ሊሆን ይችላል ብለው የሚያስቡትን ምክርና አስተያየት በተለያዩ ህዝባዊ መድረኮች ሲገልፁ መቆየታቸውና አሁንም ትልቅ መነጋገሪያ አጀንዳ ሆኖ እንደሚገኝ እሙን

ይህ የህዝብ ግፊትና እሮሮም ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየን ሶስት ነገሮችን ነው። አንደኛ የህዝቡን መሰረታዊ ፍላጎትና ችግር ተቃዋሚ ሐይሎች ከሚያራምዱት አላማና ተግባር ጋር ሲነፃፀር ፈፅሞ የማይገናኝ ለየቅሉ መሆኑን ነው። ሁለተኛ ከጊዜ ወደ ጊዜ ጋሃድ እየሆነ

የመጣው የህዝቡን ንቃተ ህሊና ከፓለቲካ ድርጅቶች በላይ ልቆ መሄዱን ነው የሚያሳየው፡፡ ተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶቹ ህዝቡን በአንድ ሀገራዊ ጥላ ስር አስተባብረው በብቃት ለመምራት ግንባር ቀደም ሆነው መገኘት ሲገባቸው ነገር ግን ከእውነታው ዓለምና ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ወደኋላ በመቅረት የሕብረተሰቡን ጭራ ናቸው እየተባለ ተደጋግሞ ከተነገረ ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ ሶስተኛው ነጥብ ደግሞ ተቃዋሚ የፓለቲካ ሐይሎች አላማቸው የፓለቲካ ስልጣን ለመያዝ ይሁን እንጂ የያዙትን የትግል መስመር በሀገሪቱ ያሉትን ስር የሰደዱ ውስብስብ ቅራኔዎችን ለመፍታትና ለመታገል የማይመጥን መሆኑን ያሳየናል፡፡ ሌላ ቀርቶ ከላይ ተደጋግመው ለቀረቡት ህዝባዊ ጥሪዎችን እንኳን እስካሁን ድረስ ምላሽ የሰጠ አንድም የፓለቲካዊ ድርጅት አልተገኘም፡፡ እንደው በደፈናው እርግማን ይመስል "<u>እኛ ላንስማማ ተስማምተናል</u>" ዓይነቱ አካሄድና መልስ ነው የምናየውና የምንሰማው፡፡ ለምን? ብለን ስንጠይቅ ደግሞ ከብዙ በጥቂቱ የምናገኘው መልስ እንደሚከተለው ነው፡፡

**የራእይ ድህነት** (የአላማ ጥራት፣ የአላማ አንድነት፣ የአላማ ፅናትና ብቃት ማነስ) ፡- በበርካታ ተቃዋሚ የፓለቲካ ሐይሎች አዘውትሮ የሚታየው ቁልፍ ችግር የራእይ ድህነት ነው፡፡ የአላማ ጥራት፣ የአላማ አንድነት፣ የአላማ ፅናትና እንዲሁም በዘመናዊ ጥበብ የተካኑ ባለራእይ መሪዎች መኖር የአንድ ፓለቲካ ድርጅትን ህልውናና ጥንካሬ የሚወስኑ መለኪያዎች ናቸው፡፡ እኔም እያልኩኝ ያለሁ የፓለቲካ ድርጅቶቹ ለምን መንግስትነት አልያዙም አይደለም፡፡ ነገር ግን የኔ ጥያቄ ትግሉ ለስልጣን ወይንም ለድል የሚያበቃው ምሶሶ የለውም ነው፡፡ ትግሉ ሞሶሶ የለውም ማለት ደግሞ በየጊዜው የሚደረገው ህዝባዊ እንቅስቃሴና የሚከፈለውን ክቡር መስዋእትነት ለጠቅላላ ድል ሳይበቃ ተዳፍኖ እንዲቀር እያደረገው ያለው ዋነኛ ምክንያት የተገኘውን ድል ጠብቆ ወደፊት የሚያራምድ ሁነኛ ባለቤት በማጣቱ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር መሰረታዊ ችግራችንን በጥልቀት አጢኖ፣ ብዙሃንነታችንንና የተፈጥሮ ሕብረ ቀለማችንን እንደ ውበት ወስዶና አዋህዶ፣ አባቶቻችንና ቅድመ አያቶቻችን በደማቸው ፅፈው የተውልንን የአደራ ቃል ኪዳን ጠብቆ፣ ሀገርንና ህዝብን ማእከል በማድረግ ሁላችንም በአንድ ሀገራዊ አላማ ጥላ ስር አስተባብሮ ታግሎ የሚያታግል ብቃት ያለው ባለራእይ መሪ ድርጅት ባለመፈጠሩና ባለመጠናከሩ ነው፡፡

ስለሀቀኛ መሪ ድርጅት አስፈላጊነት ስንናገር በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ውስጥ እንደነ መድረክ፣ አንድነት፣ ሰማዊያዊ፣ መኢአድ፣ ኢደፓን ጨምሮ በየቀኑ እንደአሸን የሚፈለፈሉ ከ60 በላይ ፈቃድ ያወጡ ድርጅቶች እንዳሉ እናውቃለን፡፡ ነገር ግን የሁሉንም ድምር እንቅስቃሴ በሀገር ደረጃ ሲታይ ለውጥ ማምጣቱስ ቀርቶ የየራሳቸውን ድርጅትዊ ህልውናም እንኳን ለመጠበቅ አቅቷቸው እየተንገዳገዱ የሚገኙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ድርጅቶች በህይወት መኖራቸውን የምናውቃቸው በምርጫ ሰሞን አካባቢ እንደ መስቀል ወፍ ብቅ ሲሉ ብቻ ነው፡፡ የአላማ ጥራታቸው ስንመለከትም አብዛኞቹ የተጠመዱት በራሳቸው ጠባብ ድርጅታዊ ፍቅር በተያያዙት ጉዳዮች ዙሪያ የሞቅ ሞቅ ስራ እንጂ ዋናውን የትግሉን አስኳልና የህዝቡን ቁስል የት ላይ እንደሆነ ገና አላገኙትም፡፡ ሌላ ቀርቶ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት እንኳን ምን ዓይነት ስርዓት እንደሆነ ባህሪውን በጥልቀት ተገንዝበው ለሱ የሚመጥን የትግል አላማና ስትራተጂ ቀርፀው የሚንቀሳቀሱ የፓለቲካ ድርጅቶች አሉን ብዬ ለመናገር አልደፍርም፡፡ በተለይም የአንድነት ሐይሎች ነን የሚሉት የፓለቲካ ድርጅቶች አላማቸውም ሆነ ባህሪያቸው ሲታይ ከአንድ ወንዝ የተቀዱ ናቸው፡፡ ከ97ቱ የቅንጅት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ እንደ አሜባ ራሳቸውን በራሳቸው እየተሰነጣጠቁ የተፈጠሩ ናቸው፡፡ አሁንም የመገነጣጠሉ ዜና ገና አላቋረጠም፡፡ ሲገነጣጠሉ ደግሞ የሚያጣላቸው የአላማ ጥራትና የመስመር ልዩነት ሳይሆን የወንበር ጉተታ ነው፡፡ የተገነጠለው ቡድንም ከበፊቱ የተሻለ ራእይና አደረጃጀት ይዞ ሳይሆን የሚመጣው ቂም በቀልን ብቻ ይዞ ስለሆነ በየጊዜው ጥላቻ ጥላቻን እየወለደ ድርጅቶቹም ማታገያ ሳይሆን መነታረኪያና ማናቆሪያ መድረክ ሆነው እንዲቀሩ አድርጓቿል፡፡ በዚህ ምክንያት ሁሉ ጊዜ ከወደ ሀገር ቤት የምንሰማው ወሬ መርዶና ተስፋ አስቆራጭ ዜና እንጂ የሚያበረታታ አይደለም፡፡ የተለያዩ የብሄር የፓለቲካ ድርጅቶች የተሰባሰቡበት መድረክም ከሌሎቹ የተሻለ አማራጭ ሐይል ሆኖ ሊወጣ ይችላል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበት የነበረ ቢሆንም በውስጠ ፓርቲ ትግሉ ገና ነጥረው ያልወጡ የጥራት ማነስ ችግር እንዳለው በየጊዜው በውስጡ ሲከሰቱ ከነበሩት አለመግባባቶች በቀላሉ ለመረዳት ይቻላል፡፡

**ትግሉ የተበታተነ መሆን** (የተበታተነ የሐይል አሰላለፍ ስትራተጂ መኖር) ፡- ሌላው ለትግሉ መዳከም ትልቁ ማነቆ ሆኖ ያለው ችግር የተቃውሞ ጎራው የተበታተነ እንቅስቃሴ (fragile movement) መሆኑን ነው፡፡ ስትራተጂ አላማህን እግቡ ለማድረስ የምትጠቀምበት የሐይል ማሰባሰቢያና የዓቅም ግንባታ ጥበብ ቢሆንም በሀገር ውስጥ ያሉት የአብዛኞቹ የፓለቲካ ድርጅቶች የራእያቸውን አድማስም ሆነ የሚቀርፁትን ስትራተጂ ሁሉንም ያገባኛል የሚል ባለድርሻ የሚያቅፍና ህዝባዊ መሰረት ይዞ የሚነሳ አይደለም፡፡ በተለይም ሀገር ተረካቢ የሆነው ወጣቱን ትውልድ ያገለለ ከመሆኑም በላይ <u>ጥቂት መሪዎች ስልጣኑን በርስትነት የሙጡኝ</u> ብለው በመያዝ <u>ወንበር እስከ መቃብር</u> ብለው የተቀመጡ ናቸው፡፡ ይህ ዓይነቱ ችግር ደግሞ መድረክን ጨምሮ በአብዛኞቹ ተቃዋሚ የፓለቲካ ሐይሎች የሚታይ በሽታ ሆኗል፡፡ ለምሳሌ ከቅንጅት ጀምሮ እየተዋለዱ የመጡት ድርጅቶች ስንመለከት በመካከላቸው የጤፍን ያህል የአላማ ልዩነት እንኳን እንደሌላቸው እየታወቀ አብሮ ተባብሮ ለመስራት አልቻሉም፡፡ ለምን ቢባል ችግሩ ያለው በሰፊው አባላቶቻቸው ሳይሆን በአንድ በኩል የየድርጅቱ መሪዎች በቂም በቀል የተጠላለፉ ናቸው፡፡ ስለትብብርና መዋሃድ ሲነሳ መሪዎቹ የሚያዩት ለሀገርና ለህዝብ ባለው ፋይዳ ሳይሆን ስለግላቸው የወደፊት ዕድል ነው፡፡ አንዳንዶቹ ትግል ማለት በአንድ ዘመን የሚጠናቀቅ የስልጣን ሽም ሽር አድርገው ስለሆነ የሚያዩት ለስርዓት ለውጥ የተዘጋጁ አይደሉም፡፡ የትግሉን ዋነኛ አላማ የስርዓት ለውጥ ለማምጣት መሆኑን ይረሱና ራሳቸውን እንደግብ ወስደው በህይወት ዘመናቸው ስልጣን ይዘው ለማየት የሚመኙ ናቸው እንጂ ለትውልድ የሚሸጋገር ስራ ለመስራት ራእዩም ሆነ ዝግጁነቱ የላቸውም፡፡ ትብብር ያስፈልጋል ሲባልም ቀድሞ በአእምሯቸው ውስጥ የሚቀረፀው ስሜት " የኔ ቦታ የት ነው? የኔ ጥቅም ይነካል ወይ? ድርጅቴ ይዋጣል፣ ጉዴ ይጋለጣል፣ ታዋቂነቴን ይቀራል፣" ወዘተ የሚሉትን የተክለ ሰውነትና የጥቅም ጥያቄዎችን ያስቀድማሉ፡፡ በዚህ ምክንያት በጋራ ጉዳይ ላይ ተባብሮና ተማምኖ ለመስራት በሚያስችሏቸው ዓበይት ጉዳዮች

ላይ ከማትኮርና ቅድሚያ ከመስጠት ይልቅ በጥቃቅን ልዩነቶች ላይ በመረባረብ ወርቃማ ጊዚያቸውን በጠጉር ስንጠቃና በእንካ ስላንቲያ እንዲያልፍ ያደርጋሉ። እውነቱን ለመናገር አንዳንዶቹ በምን እንደሚለያዩና በምን እንደሚገናኙም ጠንቅቀው የሚያውቁትም አይመስለኝም። ስለዚህ ስትራተጂው የሚያገለግለው የትግሉን አላማ፣ ሰፊው የድርጅቱን አባላትና ህዝቡን ሳይሆን ከላይ ድርጅቱን አንቀው ለያዙት መሪዎቹን ነው።

**እርስ በርስ አለመተማመን ፦** በኔ አመለካከት ብዙውን ጊዜ በተቃዋሚ የፓለቲካ ሐይሎች መካከል መተባበርና መረዳዳት እንዳይፈጠር ምክንያት ከሆነው አንዱ አለመተማመን የፈጠረው የስጋት ድባብ ነው። አለመተማመን እንዲፈጠር ካደረጉት ምንጮች ደግሞ ሶስት ናቸው። አንዱ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ሆን ብሎ የፈጠረው የለያይተህና አናቁረህ ግዛ ፓሊሲ ነው። ሁለተኛው ትምክሕተኛነት የፈጠረው የአውራነት አመለካከት ነው። ሶስተኛው ደግሞ ጠባብ ድርጅታዊ ፍቅር የፈጠረው የስጋት መንፈስን ነው። እነዚህ ጣምራ አመለካከቶች ምናልባት ደረጃቸውን ይለያይ ይሆናል እንጂ ሶስቱ ለሀገራችን ድህንነትና ለህዝባችን አንድነት እኩል አደጋዎች ናቸው።

ተደጋግሞ እንደሚታየው የአንድነት ሐይል ነን በሚሉት የፓለቲካ ሐይሎችና በብሄር ድርጅቶች መካከል አወዛጋቢ ሆኖ የሚታየው ዋናው ችግር በብሄር ብሄረሰቦች መካከል ሊኖር የሚገባው በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ አንድነትን በአግባቡ የመረዳትና ያለመረዳት የፈጠረው ስጋትና መደናገር ነው ብዬ አምናለሁ። ሁለቱን ሐይሎች የብሄር ብሄረሰቦችን ጥያቄ የሚመለከቱት በተዛባና በሀገሪቱ ውስጥ ካለው ታሪካዊ እውነታ ውጭ ነው። የአንድነት ሐይሎች ነን የሚሉት ተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች ኢትዮጵያ እኩል መብት ያላቸው የ80 ብሄር ብሄረሰቦች ሀገር መሆንዋን ይረሱና መጀመሪያ ራሳቸውን እንደ አውራ ፓርቲ፣ እንደ አንደኛ ዜጋ፣ እንደ ኢትዮጵያዊነት ሰጪና ከልካይ፣ ወይም እንደ ወሳኝ አውራ ብሄር አድርገው በማስቀመጥ ሌላውን እንደ መጤ፣ እንደ አናሳና እንደ ሚሚያ አድርገው በመውሰድ የብሄር ብሄረሰቦችን ጥያቄ የጎጥና የጎሳ ፓለቲካ እያሉ ሲያናንቁትና ሲፀየፉት ይታያሉ። አንዳንዶቹም በተለይም በቅርቡ እየተዛመተ የመጣው አፍራሽና በታኝ አመለካከት ሌላውን ብሄር ብሄረሰብ ወደ ጎን በመተው "አማራና ኦሮሞ ከተባበሩ በቂ ነው" የሚሉ ቡድኖች ብቅ ብቅ ማለት መጀመራቸው ነው። ከዚሁ ትዕቢተኛነትና የተዛባ አመለካከት በመነሳት በሁሉም መስክ የአንበሳ ድርሻን ለመያዝ ይፈልጋሉ። ለምሳሌ ተባብሮ ለመስራት በሚደረጉ ሙከራዎ በመቻቻል፣ በመከባበርና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ራሳቸውን እንደ አውራ ሌላውን እንደ አጃቢ ያስቀምጡና "ኑ ወደኛ ተጠጉ ወይም እኛን ምሰሉ" የሚለው ሃሳብ ያስቀድማሉ። ይህ ዓይነቱ አመለካከት ደግሞ የሚያቀራርብ ሳይሆን የሚበትን ስለሆነ ተቀባይነት አይኖረውም።

ሌላው በአንድነት ሐይሎች ነን የሚሉት ተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች የሚታየው ትልቅ ስህተት የብሄር ብሄረሰቦችን የሙብት ጥያቄ የራሳቸውም ጉዳይ እንደሆነ አድርገው አይመለከቱትም። ጉዳዩን ለብሄር ድርጅቶች ብቻ የሚተው ሳይሆን እነሱም የትግላቸው አካል አድርገው በመውሰድ ለችግሩም ሆነ ለመፍትሄው ሃላፊነትንና ግዴታን እንዳላቸው አድርገው አያምኑም። በአንፃሩ እነሱ እንደ አንደኛ የአንድነት ጠበቃ ሌላው ብሄር ብሄረሰብ ግን እንደ ገንጣይና ለሀገሩ አንድነትና ዕድገት የማያስብ ጠባብ አድርገው ነው የሚፈርጁት። ለምሳሌ አንድነት ከመድረክ ሲገነጠል እንደ ትልቅ መለያያ አጀንዳ አድርጎ ሲሚጎትበት የቆየው ራሱን እንደ አውራ የፓለቲካ ፓርቲ አድርጎ በመቁጠር በሀብት ምንጭም ሆነ በሰው ሐይል ከሌሎች አባል የብሄር ድርጅቶች የጎለበትኩ ነኝ ብሎ ስለሚያምን በሁሉም ጉዳዮች በአመራርም ሆነ በሃሳብ የበላይነት እንዲኖረው ይፈልግ እንደነበር ይታወቃል። ሌላ ቀርቶ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የነበሩትን ፅሕፈት ቤቶ ሌሎች የመድረክ አባል ድርጅቶች ዘወር ብለው እንዳያዩዋቸው የሚያደርግ አመለካከት ነበረው። ከዚህም አልፎ ሁሉንም የመድረክ አባል ድርጅቶች በአንድ ጀምበር ወደ አንድነት ፓርቲ ካልተቀየራችሁ ከብሄር ድርጅቶች ጋር አብሬ አልሰራም በሚል ነበር ሰበብ አስባብን ፈልጎ የተገነጠለው። ከተገነጠለ በኋላም አልሆነለትም እንጂ ቂሙን ለመወጣት በተለያየ መልኩ መድረክን ለመበተንና ለማዳከም እንቅልፍ አጥቶ ሲሰራ ቆይቷል። ሌሎቹ እንደ መኢአድ፣ ኢዴፓና ሰማያዊ የመሳሰሉትም ደረጃው ይለያይ እንደሆነ እንጂ አመለካከታቸውና ዕጣ ፋንታቸው ተመሳሳይ ነው።

የብሄር ድርጅቶችም በበኩላቸው ከሚወቀሱበት አመለካከት አንዱ የያዙትን አላማ፣ የሐይል አሰላለፍና ያደረጃጀት ስትራተጂ ሀገራዊ ዓቅምን የሚበታትን ነው። የተነሱበት አላማም በርእዮተ ዓለም ላይ የተመሰረተ ሳይሆን በክልልና በቋንቋ ላይ የተመሰረተ ነው የሚሉት ትችቶች ተደጋግመው ይቀርባሉ። የእንቅስቃሴያቸው አድማስም የታጠረው በሀገር ደረጃ ሳይሆን በአንድ ቋንቋና ክልል አካባቢ ስለሆነ ቅድሚያ የሚሰጡት ለሀገራዊ ጉዳይ ሳይሆን ለዚያው አካባቢ ብቻ ነው በማለት ተደጋግመው ከሚቀርብላቸው ጥያቄዎች ውስጥ "ሁሉም ለየራሱ ክልል ብቻ የሚንቀሳቀስ ከሆነ የሀገርን ጉዳይ ባለቤቱ ማን ነው? ቅድሚያ ለየክልላችሁ የምትሰጡት ከሆነ ሀገር ከሌለ የምታደርጉትን የብሄር ትግል መጨረሻው ምንድን ነው? የብሄር ድርጅቶች ስለሌላው ኢትዮጵያዊ ጉዳይስ ሃላፊነት የላቸውም ወይ? ሌላው ህዝብ በባርነት እየኖረ አንድ ክልል ብቻውን ታግሎ ብቻውን ነፃ ሊወጣ ይችላል ወይ?" የሚሉትን ናቸው።
በማጠቃለል የተቃውሞ ሐይሉን የተዳከመ፣ የተበታተነና የተመሰቃቀለ በመሆኑ በይበልጥ የተጎዱት ህዝቡንና ታጋይ ሐይሉን ናቸው። የፓለቲካ ድርጅቶቹ ተነጣጥለው በየተራ ለጥቃት፣ ለወከባና ላለአላስፈላጊ መስዋእትነት እንዲዳረጉ ምክንያት ሆኗል። የትግሉ ውጤትም እየጎለበተ ሳይሆን እየባሰ እየመነመነ፣ እየተሰላቸ፣ እየቀጨጨና እየመረረ በመሄዱ ብዙ ሰው ተስፋ እየቆረጠ ከትግሉ ጎራ እንዲሸሽ አድርጎታል። አምባ ገነኖቹም ያለውን ክፍተትና ደካማ ጎን በመጠቀም ተቃዋሚ ሐይሎችን እርስ በራሳቸው እያባሉና እያናከሱ በማሀሉ እነርሱ ተጠቃሚ እየሆኑ ለመኖር ጥሩ አጋጣሚ ተፈጥሮላቿል። በተጨማሪም የተቃውሞ ጎራው መዳከምና የተበታተነ መሆን በህዝቡም ሆነ በውጭ ዓለም ማሕበረሰብ ዘንድ ሊኖረው የሚችል ተሰሚነት፣ ተሰፋና አሜኔታም እየቀነሰ በመሄዱ የፋይናንስም ሆነ የሰው ሐይል ምንጩ የደረቀ እንዲሆን አድርጎታል።

## ችግሩን ከስረ መሰረቱ ለመፍታት ምን መደረግ አለበት?

የችግሩም የትግሉም ምንጭና ባለቤት እኛው እስከሆን ድረስ መፍትሄውም ከሌላ የውጭ ሐይል የምንጠብቀው ሳይሆን በኛው በራሳችን እጅ ላይ ነው ያለው። ከላይ በመጠኑም ቢሆን የተጠቀሱትን ችግሮች ያጤነ ሰው መፍትሄውም ምን መሆን እንዳለበት ይስተዋል ብዬ አልገምት። ችግርህን ማወቅ የመፍትሄ ግማሽ መንገድ ነው እንደሚባለው ሁሉ ከላይ የተጠቀሱትን ሃሳቦች መጀመሪያ ቁልፍ ችግራችን (Root cause) ምንድን ነው ብለን አንጥረንና ቆፍረን ለማውጣት እንድንችል አስተዋፀዖ ይነሯል የሚል እምነት አለኝ። አንድ ሰው በሽታው ምን መሆኑን በትክክል ካልታወቀ መድሃኒቱን ምን እንደሆነ ለማወቅ እንደሚያስቸግር ሁሉ በአንድ የፓለቲካ ድርጅት ውስጥም ያሉትን መሰረታዊ ችግሮች በመላ አባላቱን ሰፊ ተሳትፎ በግልፅ ነጥረው ካልወጡና ካልተወቁ በስተቀር በምንም መልኩ መፍትሄውም ለማወቅ አይቻልም። ስለዚህ ቁስሉን መደበቅ  መድሃኒቱንም መደበቅ ስለሚሆን አስቀድመን ችግሮቻችንን ለይተን ማወቅ ቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል። ችግሮቹን ውስጡ ለቁስ ብሎ ሾላ በድፍን ተደባብቆ መሄድ እየዋለ እያደረ በሽታው ወደ ካንሰርነት መለወጡ አይቀርም።

በኔ አመለካከት ከላይ የተጠቀሱትን ዋና ዋና ችግሮች ጨምቀን ስናያቸው ማነቆ (bottle neck) ናቸው ብዬ የማስበው ዝቅተኛ ሀገራዊ ንቃተ ህሊና እና ኋላቀር የፓለቲካ ባህሎች የወለዱት የራእይ ድህነት ነው። ስለዚህ ተቃዋሚ የፓለቲካ ሐይሎች ከገቡበት ኋላቀር የፓለቲካ አዙሪት (vicious circle) ሰብረው ለመውጣት ይችሉ ዘንድ መጀመሪያ ራሳቸውን መለውጥ ተቀዳሚ ተግባር ነው ብዬ አምናለሁ። ምክንያቱም ለራሳቸው የለውጥና የዴሞክራሲ አርአያ ለመሆኑ የሚያበቃ ራእይ የሌላቸው የፓለቲካ መሪዎች በምንም መልኩ የለውጥ ሐይሎች መሆን አይችሉም። መጀመሪያ ለራሳቸው በአንድነት ተባብሮ ለመስራት መስዋእትነትን ለመክፈልና ተምሳሌት ሆነው ለመገኘት ዝግጁነቱንና ፍላጎቱን የሌላቸው የፓለቲካ መሪዎች ፍፁም የአንድነት ሐይልና ጠበቃ መሆን አይችሉም። በሌላ አገላለፅ የ16ኛው ከፋፍለህ ግዛ የመሳፍንት ዘመን አመለካከት የያዙት ፓለቲከኞች የ21ኛውን ክፍለ ዘመን ትውልድን በምንም መልኩ የፓለቲካ መሪ ለመሆን አይችሉም። ስለዚህ መፍትሄው ከአግላይ፣ በታኝና ስክተሪያን ከሆነው የፓለቲካ አካሄድ በመውጣት በተለይም የነገውን ሀገር ተረካቢ የሆነው ወጣቱን ትውልድ የሚመጥን ራእይ የያዙት ሀገራውያን ሐይሎች መሰባሰብ ዋል እደር የማይባል ጉዳይ ነው።

ሌላው ለችግሮቻችን መፍትሄና ተቀራርቦ ለመስራት በር ከፋች የሚሆነው የቅራኔ አፈታትና የይቅርታ መንፈስ ባህላችንን ማዳበር ነው። የሰለጠነ የቅራኔ አፈታት ማለት የነቃ ሕብረተሰብ መለያ እሴት ብቻ ሳይሆን በአሁኑ በግሎባላይዘሽን ዘመን ህዝብ ለህዝብ፣ መንግስት ለመንግስት፣ ቢዝነስ ለቢዝነስ፣ ወዘተ እያስተሳሰረ ያለው የሰጥቶ መቀበል መርህም ጭምር ነው። በሰለጠኑ ሀገሮች የሃሳብ ልዩነት መኖር ፀጋና የዕድገት መሰረት ተደርጎ ነው የሚታየው። ምክንያቱም የተለያዩ ሃሳቦች ሲፋጩ ጥራትና ስለት ያለው ውጤት ያስገኛሉ። እንደኛ ኋላቀር የፓለቲካ ባህል ባለበት ሕብረተ ሰብ ደግሞ ልዩነት ወይም ቅራኔን የሚፈታው በሰለጠነ መንፈስ በጠረጴዛ ዙሪያ ሳይሆን በዱላ ወይም በመጠፋፋትና በመደማሰስ ላይ የተመሰረተ ነው። ያለፈው የአርባ ዓመት ታሪካችንም ይህንን ነው ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየን። የኔ ጥያቄም በተቃዋሚ ድርጅቶች መካከል ለምን የራእይ ልዩነት ተፈጠረ ወይም ለምን የተለያዩ ድርጅቶች ተቋቋሙ አይደለም ስጋቴ። ነገር ግን ያለፈውን የመናቆር፣ የመጠፋፋትና የመደማሰስ ታሪክ እንደገና ተመልሶ እንዳይመጣ ነው። ስለዚህ ችግራችንን ለማስወገድ በቅድሚያ ኋላቀር የቅራኔ አፈታት ባህላችንን አስወግደን ለሀገርና ለህዝባችን ድህንነት ሲባል በመቻቻል፣ በሰጥቶ መቀበልና በሰከነ መንፈስ ላይ የተመሰረተ የውይይት መድረክን በመፍጠር ልዩነትን ይዞ አብሮ መስራትን መለመድ አለበት የሚል ነው። ፓለቲካና ዴሞክራሲ ማለትም ዋናው ቁም ነገሩ ልዩነትን በሰለጠነ አገባብ የማስተናገድና ተቻችሎ አብሮ የመኖር ጥበብ ነው። ስለዚህ ያለፈውን ቁርሾ እየቀሰቀሱ የታሪክ እስረኛ ሆኖ ከመኖር ይልቅ የነገ ተስፋና የይቅርታ ሰው ሆኖ መገኘት ብልህነት ነው ብዬ በፅናት አምናለሁ። ተወዳድሮ ማሸነፍ የሚቻለውም በልጠው ሲገኙ ብቻ ነው።

በማጠቃለል አሁን ባለንበት አሳሳቢ የታሪክ አጋጣሚ (historical juncture) ተቃዋሚ የፓለቲካ ሐይሎች በጋራ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ተባብረው መስራት አለባቸው ስንል አንደኛ ለጌጥ ሳይሆን የህልውናቸው መሰረትም ስለሆነ ነው። ተበታትነው በተናጠል እየተቀጠቀጡ ከሚኖሩ ይልቅ ሕብረት ፈጥረው በጋራ ቢንቀሳቀሱ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ዓለም ተሰሚነትና ተፅዕኖ ፈጣሪ ለመሆን ይችላሉ። የፋይናንስና የሰው ሐይል ምንጫቸውም ሆነ ድርጅታዊ ዓቅማቸው ይጎለብታል። ከሞቅ ሞቅ ፓለቲካ ወጥተው ለመጪው ትውልድም መሰረት እየጣለ የሚሄድ ይሆናል። ሌላው ተባብሮ የመስራትና ጠንካራ የመሪ ድርጅት አስፈላጊነት አንገብጋቢ እንዲሆን ያደረገው አሁን ያለው የሀገራችን ሁኔታ ከማንም ጊዜ በላይ ብቃት ያለውና የተቀናጀ ጠንካራ የፓለቲካ አመራር የሚጠይቅ ፈታኝ ጊዜ በመሆኑ ነው። በቅርቡ በተለያዩ አካባቢዎች የተነሳው የህዝብ ዓመፅም ሚያመላክተው የሁኔታው አሳሳቢነትንና አንገብጋቢነትን ነው።

**ከይኩኖ መሰፍን**

sgbtsait@gmail.com

ለምትልኩልኝ ገንቢና ሚዛናዊ አስተያየት በቅድሚያ ከአክብሮ ጋር አመሰግናሁ